<u>**የሚያነቡ እግሮች   በግርማይ አብርሃ**</u>

<u>**ግምገማ   በበልጅግ አሊ**</u>



"የሚያነቡ እግሮች" የሚል እውነተኛ ታሪክ የሆነ መጽሐፍ በግርማይ አብርሃ ተጽፎ አዲስ አበባ ውስጥ በግንቦት 2002 ዓ.ም. ለንባብ በቅቷል ። መጽሐፉ ትኩረት የሚሰጠው ፋሽስታዊ የነበረው የደርግ መንግሥትና ከሥሩ የተኮለኮሉት አድርባዮች የፈፀሟቸው ፋሽስታዊ ተግባሮች ላይ ነው ። መጽሐፉ በተለያዩ እስር ቤቶችና የማሰቃያ ተቋሞች ውስጥ የሃገሪቱ ዜጎች ላይ ይደርስባቸው የነበረውን አስከፊ የሆነ ሥቃይ፣ መከራና ፣ግፍ በመረጃ በመደገፍ ለንባብ ያበቃ የታሪክ መዘክር ነው።በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሰው ደርግ በሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት እንደ አሸን የተፈለፈሉትን እስርቤቶች በውስጣቸው የነበረውን ሥቃይና መከራ ብቻ ሳይሆን እሥረኞቹ ሥቃዩን ለመቋቋም ፣ ችግራቸውን ለመፍታት፣ ያንን የመከራ ጊዜ ተባብረው ለማለፍ  የተጠቀሙበትን ዘዴዎች፣ ያቋቋሚቸውን ኮሚቴዎች ፣ የወሰዷቸውን እርምጃዎች ቁልጭ ተደርጎ ቀርቦ ይገኛል ።

ይህንን መጽሐፍ እንደ ታሪክ መረጃ ልንቀበለው የሚገባ ነው ። በደርግ ሥርዓት በተለያዩ እስር ቤቶች ውስጥ የታሠሩትን ፣ የተገረፉትን ፣ የተገደሉትን እንዲሁም የተፈቱትን በማስረጃ በተደገፈ የስም ዝርዝር ማንንም ሳይወግን፣ የተለያዩ የፖለቲካ አቋም ያላቸውን አድልዎ ሳያደርግ፣ በመዘርዘር የነበረውን ሁኔታ እንዳለ ለማስቀመጥ የተደረገ ሙከራ ነው ።

በአሁኑ ወቅት በደርግ መንግሥት ወቅት የነበረውን ሁኔታ የሚጻፉት መጽሐፍት በደርግ ዘመን ሥልጣን ላይ በነበሩ ሰዎች ነው። (ለምሳሌ ተስፋዬ ርስቴ - ምስክርነት በባለሥልጣኖቹ አንደበት  ፣ ዘነበ ፈለቀ - ነበር፣ ተስፋዬ መኮንን ይድረስ ለባለታሪኩ). . . )እነዚህና እነዚህ የመሳሰሉ ደራሲዎች ደግሞ ያደረሱትን በደል ተገቢ ነበር በማለት ለማካካስ ያልሆነ መረጃ መጻፍ የተለመደ ሥራቸው ሆኑዋል ። ይህ መጽሐፍ ግን በእስር ቤት ውስጥ ለሰባት አመታት በነበረ ግለሰብ ሲሆን የእሥረኞችን የቀን ተቀን ኑሮ ፣ የደረሰባቸውን መከራ አብሮ በመካፈሉ በአሉታ ሳይሆን ራሱ ያሳለፋቸውን፣ የዓይን ምሥክር የሆነባቸውን የመከራ ዘመኖች በጽሁፍ አቅርቦታል ። በዚህ መጽሐፍ የነበረውን ታሪክ ስንመረምረው ስለዚያ ዘመን እሥረኞች በራሳቸው አንደበት ሲነገርና በአሳሪዎቹ ሲተረት የተለያየ መሆኑን ለማወቅ ይረዳናል ።

ይህ የግርማይ አብርሃ መጽሐፍ በአሁኑ ጊዜ ታሪከን በማጣመም፣ ደርግን መልካም ተግባራት እንደፈፀመ መንግሥት ፣እንደ ሃገር ወዳድ ፣ ድንበር አስጠባቂ አድርገው ሊያቀርቡ ለሚፈልጉ፣ በመጽሐፍ ደርሰው እውነትን ለመካድ ለሞከሩት በሙሉ እውነቱን በማጉላት፣በመረጃ የተቀነባበረ መጽሐፍ በማቅረብ ለሚቀጥለው ትውልድ ትምህርት ሲሆን የሚችል ታላቅ ንብረት ነው ።

በአሁኑ ወቅት በየፓልቶኩ ፣ በየጋዜጣው ፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እውነተኛ ታሪክን በማጣመም ስለ ደርግ ጥሩነት፣. በተለይም ደርግ የተዋጋው የአንድነት ጠላቶችን፣ ተገንጣዮችን፣ ፀረ ሕዝቦችን ፣ . . .  ብቻ ነው እያሉ ለሚሰብኩ ሁሉ "የሚያነቡ እግሮች" በዚህ በግፍ አገዛዛቸው የጨፈጨፉት የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ብቻ ሳይሆኑ(እነሱም ይገደሉ የሚል ሕግ ባይኖርም ) ንፁሃን ዜጎች ፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ንጉሳዊያን ቤተሰቦች ፣ ሽማግሌዎች ፣ አሮጊቶች ፣ ሕፃናት ባጠቃላይ  በማንአለብኝነት የተደረገ ጅምላ ጭፍጨፋ እንደነበር ግልፅ አድርጎ ያሳየናል ።

ቀይ ሽብር ለብዙ ዜጎች በ1969 ጀምሮ እስከ 1971 ዓ. ም *( **በዚህ ጽሁፍ ላይ ያለው የዘመን አቆጣጠር ሁሉ የኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ነው** ) መጨረሻ ድረስ የነበረ ግድያ ነው ብለው ያምናሉ ። ይህ ግን ትክክል አይደለም ። "የሚያነቡ እግሮች" ጸሐፊ የመጨረሻው በኢሕአፓ አባላት ተጠርጥረው ቀይ ሽብር  የተካሄደው መስከረም 24 ቀን 1978 መሆኑን ከእነ ስም ዝርዝራቸው አቅርቦታል ። በአሁኑ ጊዜ ቀይ ሽብር "የነጭ ሽብር" ምላሽ ነው ብለው የሚራቀቁ የደርግ ደጋፊዎች ቀይ ሽብር -  ደርግ ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት በሙሉ ያላቋረጠ እንቅስቃሴ እንጂ " ነጭ ሽብር " ብለው ለፈጠሩት ተረት ተረት መልስ አይደለም ።ቀይ ሽብር  በተቃዋሚዎቹ ብቻ ላይ ሳይሆን  በሃይማኖት አባቶች፣**(ከኦርቶዶክስ ፣ከእስልምና ፣ ከየዮሆዋ ምስክሮች ዝርዝር ከነ ፎቶ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል)** በሕጻናት ፣ በነጋዴዎች**(የተገደሉ ነጋዴዎች ሥም ዝርዝር መጽሐፉ ውስጥ ይገኛል)** እንደሆነ ሊክዱ ይፈልጋሉ ። ከዚህ በታች የሚታየው መረጃ ይህንን ግልጽ አድርጎ ያሳየናል ። በ1978 ዓ.ም "ነጭ ሽብር " የሚባለው ተረት ተረት ነበር ተብሎ እስካልታመነ ድረስ ወይም ደግሞ የዮሆዋ ምስክሮች "ነጭ ሽብር" ላይ ተሳትፈዋል እስካልተባለ ድረስ ተረት ተረቱ የማሞ ቂሎን ታሪክ ይመስል  መሳቂያ ነው የሚሆነው ።

በተለይም ደግሞ ቀይ ሽብር "የነጭ ሽብር " ውጤት ነው ብለው ለሚሰብኩ የደርግ ካድሬዎች ቀይ ሽብር እስከ 1978 ዓ.ም  **(ደርግ ሊወድቅ አምስት አመት)** በፊት ይካሄድ እንደ ነበር ጸሐፊው በመረጃ አስቀምጦታል ። ለመረጃ ያህል በመጽሐፉ ውስጥ መስከረም 24 ቀን 1978 የተፈጠረውን ሁኔታ እንመልከት፡ -

> **ዕለቱ ዓርብ መስከረም 24 ቀን 1978 ዓ.ም. ነበር ። የማዕከላዊ የምርመራ ድርጅት ሰዎች ግቢው ከደረሱ በኋላ የስም ጥሪ እንዲተላለፍ ተደረገ ። ጥሪው ግን የተለመደ የጋቢና የዋራንት ጥሪ መልክ የያዘ አልነበረም ።እገሌ፣እገሌ ሙሉ ስማቸው በግቢው**

ከልሎች ከተሰተጋባ በኋላ ወደ ተጠሩበት የወይኒ ቤቱ ሥፍራ ሄደው ሁሉም " ለነገ ጥዋት ዕቃዎቻችሁን አዘሃጅታችሁ ጠብቁ " ተብለው ወደ ነበሩበት ማደራሪያቸው ተመለሱ ።

ይህ አሠራር ለየት ያለ በመሆኑ መላው እሥረኛ ታወከ ። የእሥረኛው ሕብረተሰብ ጥርጣሬ ውስጥ የከተተው የተጠሩት ሰዎች ወዲያውኑ አለመሄዳቸው እና ተመልሰው እንዲያድሩ በመደረጉ ብቻ አልነበረም ። እንዲረበሽ ያደረገው የተጠሩት እሥረኞች ማንነት ፣ የፖለቲካ ታሪካቸው ፣ ድርጅታዊ ስብጥራቸው ነበር ።

የተጠሩት ሰዎች አብዛኞቹ ለሰባትና ለስምንት ዓመታት የታሠሩ የኢሕአፓ አባላት ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ የህወሐት ፣ የህግሐኤ እንዲሁም ደግሞ " ከሁሉም በላይ አብዮቱ " የሚለውን የደርግ መንግሥት መፈክር አናስተጋባም " ከሁሉም በላይ እግዚሐቤር ነው " ያሉ የዮሆዋ ዊትነስ ሃይማኖት ተከታይ እሥረኞች ናቸው ።በዚህ ወቅት የወይኒ ቤቱ ማህበረሰብ የተጠሩትን ሰዎች ለማጽናናትም ሆነ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት የተቸገረበት ነው ። ከተጠሩት አብዛኞቹ ሰዎች ፊት የሚነበብ ጥርጣሬም ሆነ የሚያፈልቁት ቃላቶችም ምሽቱ ድብርት የሰፈነበት አደረገው ።

እንደተባለውም በነጋታው ቅዳሜ ቀን ተጠርተው ያደሩት የፖለቲካ እስረኞች በድጋሚ ተጠርተው ወደ ማዕከላዊ የምርመራ ድርጅት ተወሰዱ ። ማዕከላዊም እንደደረሱ በቃል እንደሚፈቱ ተነግሯቸው ወደ አንድ አዳራሽ ተሰበሰቡ ። ከዚያ በኋላ ግን ሁለት ሁለት ሆነው እየተጠሩ በሰለጠኑ ወታደሮች አማካኝነት እየታነቁ ተገደሉ ። በዚሁ ዕለት ለዕልፈት የተዳረጉትም በጠቅላላው ቁጥራቸው 40 የሚደርስ እሥረኞች ሲሆኑ የሚከተሉት ስሞች ይገኙባቸዋል ።

1. የኢሕአፓ (የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ) አባላት የተባሉ

ጌታቸው ኩምሳ
አምሃስላሴ ጌታነህ
ዮሐንስ ግርማቸው
ንጉሴ እውነቱ
ከበረ ኃይሌ
ቴዎድሮስ
ማህዲ ከማል
ጌታቸው አሰፋ
ሱሌማን መሃመድ
ቴዎድሮስ አሰፋው
ዘሪሁን በንቲ
አስናቀ ጌታቸው
ዘውዱ ኃይለሚካኤል
ተሻለ ወንድሙ
አሰፋ ረጋሳ
ሰለሞን ግርማ
ተስፋዬ ገብረማርያም
ዓለም ኪዳኔ

2. የህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ አባላት የተባሉ

የማነ ብርሃን ብርሃነ
ወልደገብርኤል ለማ

3. የህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ አባለት የተባሉ

ዛይድ በላይ
ኤፍሬም ንርአዮ
ገብረእግዚአብሄር የማነ
ተኽስተ ሓዲሽ

4. የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ አንድነት አባላት የተባሉ (ማዕከላዊ ምርመራ የነበሩ )

ደጃዝማች አሰጋኸኝ አርአያ
ማህተመወርቅ ካሳሁን
አከሊሉ መዋኢ
ውቤ ገብረዮሐንስ

5 የዮሆዋ ምስክሮች

ወንድሙ ደበላ
ገብረዮሐንስ አድሃኖም
ካሣ ገብረመድህን
እሸቱ ምንዳ
ካባ አያና
አደራ ተሾመ

**የሚያነቡ እግሮች ገጽ 267 – 271**

እነዚህ ከዚህ በላይ ስማቸው የተዘረዘረው የሞት ፍርድ የተፈፀመባቸው በታሰሩ በስምንትና ዘጠኝ ዓመታቸው ነው።ብዙዎቹ እንፈታለን ብለው ተስፋ አድርገው በከርቸሌ ውስጥ የነበረው እስር ቤት ገብተው ነበር ። የወጣትነት እድሜቸው ላይ የፈረዱባቸው ዛሬ በነጻ ዓለም እየተዝናኑ የገዳይነት ገድላቸውን እየጻፉ በሚያገኙት የደም ገንዘብ

እየተዝናኑ ነው ። የገዳዮቹም ሆነ የተገዳዮቹ ስም ዝርዝር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በብዛት ሲገኝ ወርቅ የሆኑ መረጃዎችን አካቶ ይዟል ።

ከሁሉ የሚገርመው ቀይ ሽብር የተጀመረው መቼ እንደሆነ ለማወቅም አዳጋች መሆኑ ነው ። ሐምሌ 6 ቀን 1968 የኢኮኖሚ አሻጥር አድርገዋል ተብለው የተገደሉት ደግሞ ምን ሊባሉ እንደሚቻል አላውቅም ። በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ስሞቻቸውና ሥርተዋል የተባለው" ወንጀል" ተጠቅሷል ።

**1. ሙኒር ከሊል ሀሰን**
**3500 ኩንታል በርበሬ ደብቋል ተብሎ**
**2. ሼክ ጀሚል ኢብራሂም**
**2500 ኩንታል በርበሬ ደብቋል ተብሎ**
**3. ተስፋኪሮስ ወልደስላሴ**
**2000 ኩንታል በርበሬ ደብቋል ተብሎ**
**4. ሐጂ አህመድ ማህመድ**
**1500 ኩንታል በርበሬ ደብቋል ተብሎ**
**5. መሐመድ ሰይድ በርሔ**
**1500 ኩንታል በርበሬ ደብቋል ተብሎ**
**6. ገዳ ገቢ**
**2500 ኩንታል በርበሬ ደብቋል ተብሎ**
**7. ባዘዘው ነጋሽ**
**200 ኩንታል ጤፍ ደብቋል ተብሎ**
**8. ደምሴ ከበደ**
**በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስተር የስኳርና የጨው ማከፋፈያ ድርጅት ውስጥ ሲሰራ ጉቦ ተቀብሏል ተብሎ**
**9. አሰፋ ካሳ**
**በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስተር የስኳርና የጨው ማከፋፈያ ድርጅት ውስጥ ሲሰራ ጉቦ ተቀብሏል ተብሎ**

**የሚያነቡ እግሮች ገጽ 118 - 119**

የገዳዮቹም ሆነ የተገዳዮቹ ስም ዝርዝር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በብዛት ሲገኝ ወርቅ የሆኑ መረጃዎችን አካቶ ይዟል ።

መጽሐፉ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው ። የመጀመሪያው ክፍል የሚያተኩረው ደርግ ሥልጣን ከወጣበት ወቅት ጀምሮ ስልጣኔን ያስጉታል ብሎ የሚጠረጥራቸውን ተቃዋሚዎች .የሚያሥርበት ፣ የሚያሰቃይበት ፣ ግድያውን የሚያስፈፅምበት ማዕከላዊ ተብሎ ይጠራ የነበረው የማሰቃያ እስር ቤት ሲሆን ፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የሚያተኩረው በአዲስ አበባ ወህኒ ቤት(ከርቸሌ) ነው ።

**"አብዮታዊ ማዕከላዊ ምርምራ ድርጅት"** ተብሎ ይጠራ የነበረው እስረኞችን የማሰቃያና የመመርመሪያ እስር ቤት የሚገኘው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከዳግማዊ ምኒልክ አደባባይ በስተሰሜን አቅጣጫ ወደ አዲሱ ገበያ በሚወስደው የበላይ ዘለቀ ጎዳና ነው ። ይህ እስር ቤት በውስጡ የምርመራ .ክፍሎችን ፣ቢሮዎችንና የማጎሪያ ሥፍራዎችን የያዘ ነበር ። ይህ በንፁሐን ወገኖች ላይ ባደረሰው ግፍ ስሙ እጅግ የገነነውና የሚፈራው የምርመራ ቦታ በኢትዮጵያውያን ላይ ያደረሰው ግፍ በሃገሪቷ ታሪክ ውስጥ ከደረሱት ጥፋቶች ሁሉ ጎልቶ የሚታይ ነው ። በተለይ በቀይ ሽብር ውስጥ የነበረውን ሁኔታ ፀሐፊው ሲያብራሩ፡

> **በማዕከላዊ እስር ቤት ውስጥ ያለው እያንዳንዱ የእሥረኛ ክፍል(ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ከ16 ካሬ ሜትር የማይበልጥ ክፍሎች) ባለብረት መዝጊያና ባለወንፊት የብረት መስኮት እንዲኖረው ሆኖ የተሠራ ነው ። . . . .**
>
> **የቀይ ሽብር እርምጃ በተፋፋመበት አመታት ግን የላይኛው ግቢ ውስጥ የሰው ልጅ ህሊና ከሚገምተው ውጭ እስረኞች አለቅጥ ታጭቀው ቁምስቅላቸውን እንዲያዩ ተደርገዋል ። በእያንዳንዱ ክፍል ቁጥራቸው ከ70 የማያንሱ እስረኞች ታጉረውበታል። ይህ የቀይ ሽብር አንዱ መገለጫ ሲሆን በምርመራ እና ግርፋት ሲዋከብና የተለያየ የሥነ ልቦና ጫናዎች ሲደርሱበት የዋለው እስረኛ በሌሊትም መፈናፈኛ በማጣት ተፈጥሯዊ የሆነውን እንቅልፍ በወጉ ማግኘት ተስኖት እጅግ የተሰቃየበት ቦታ ነው ።**
>
> **የሚያነቡ እግሮች ገጽ 4-5**

አንባቢያንን ስለ ቦታው ጥበት እንዲገባቸው ከፈለጉ 4ሜትር በ4ሜትር የሆነ ቦታ ለክተው ስንት ሰው ማስተኛት ወይም ማቆም ይቻል እንደሆነ ሊሞክሩት ይገባል ። ይህ የእሥር ቤቶች ሁኔታ በሌሎችም እሥር ቤቶች ውስጥ ቢሆን የተለየ አይደለም ። በደርግ ጽህፈት ቤት ውስጥ የነበረውን ለመመስከር ያህል ከዚህ የከፋ ነበር ። ጠቅላላው እስረኛ በግርፍ ብዛት መቆም የማይችል ሆኖ ሳለ በዛ ጠባብ ክፍል ውስጥ እንደ ሰርዲን ተጠቅጥቀን በማደር እዛው እስር ቤት ውስጥ የሞቱ እንደነበሩ የምናስታውስ አለን ።በእነዚህ ጠባብ ክፍሎች ውስጥ የታሰሩት እስረኞች ግማሾቹ እግሮቻቸው በግርፋት ብዛት የቆሰሉ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ከእግራቸውም አልፈው ሰውነታቸው በእሳት፣ በዘይት የተቃጠሉ

፣የተጠበሱ ነበሩ ። አብዮታዊ ማዕከላዊ የምርመራ ድርጅት ከእስረኞቹ ምሥጢርን ለማውጣት የሚጠቀምበት ዋናው መንገድ የተለያዩ የማሰቃያን ዘዴዎች እያፈራረቁ መጠቀም ነው ።

በቀበሌ እሥር ቤት ውስጥ ከዚህ የተለየ ሁኔታ አልነበረም ። የደርግ ሥርዓት ተጀምሮ እስከሚያለቅ ድረስ እስር ቤቶች ባዶ ሆነው ባያውቁም በተለይ ከ1968 - 1978 ድረስ ይታይ የነበረው አስቃቂ ሁኔታ መገመት ከሚቻለው በላይ ነበር ። መጽሐፉ በተከታታይ ባሉ ክፍሎቹ ያስቀመጠው በወቅቱ ስለተከፈለው መስዋዕትነትና በዚያውም አንፃር ስለታየው ክህደት ነው ። በሁሉም እስር ቤት ውስጥ ከመንግሥት ጋር የቆሙ ፣ የደርግን ትዕዛዝ የሚያስፈፅሙ እስረኞች እንደነበሩ የሚታወስ ነው ። በተለይም በወንጀል የታሰሩትን ቦዘኔዎች ለፖለቲካ መጠቀም በቀይ ሽብር ወቅት የደርግ ዋንኛው ባሕሪው ነው ። ከቦዘኔዎቹ ባሻገር የፖለቲካው ውጤት የነበረው በቀይ ሽብር ወቅት በተለይም በኢሕአፓ ውስጥ የተፈጠረውን አንጃ የፈፀመውን ጭፍጨፋ ጉልህ ሆኖ ይታይ እንደነበር ተጠቅሷል።በተለይ ደግሞ "ከአብዮቱ ባቡር " በየፈ**ር**ማታው የወረዱ የደርግ ባንዳዎች በእስር ቤትም ምንም እንኳ ብንታሰር አሁንም የአብዮቱ ወገን ነን በማለት ያደረሱት ግፍ ሰፋ ያለ ነው ። የሚያነቡ እግሮች ይህንን በተመለከተ የሰጠው ምሥክርነት በተለያዩ ገጾች ይገኛሉ ። ለመጥቀስ ያህል ፡ -

> *በርካታ ኢትዮጵያውያን ለቆሙለት ዓላማ ፀንተው ታግለዋል ። በአብዮታዊ ዲሲፕሊን ፀንተው ፏሽስቶችን በጀግንነት ተጋፍጠዋል ። ለድርጅታቸው ሕልውና ለጓዶቻቸው ደህንነት ፣ ብሎም ለሰው ልጅ ክቡር ሕይወት ሲሉ በደርግ መርማሪዎች ከመሰቃየታቸውም በላይ መተኪያ የሌላትን ውድ ሕይወታቸውን ከፍለዋል ። ይህ የዓላማ ጽናት ከሚያራምዱት የፖለቲካ እምነት ፣ድርጅት ፍቅር ፣ከሰብአዊ አመለካከትና ቅንንት የመነጨ ነበር ።*
> *በተቃራኒው ደግሞ በደርግ ሥር ተንበርክከው ፣ የቆሙለት ጎራ በመናድ ክህደት የፈፀሙ ፣ የድርጅታቸውን ሚስጥርና ጓዶቻቸውን አሳልፈው የሰጡ እስረኞች ነበሩ ። የራስን ሕይወት ለማኖር ሲባል ከደርግ መርማሪዎች በማይተናነስ መልኩ በትግል ጓደኞቻቸው ላይ በማሴር ጉዳት ያደረሱ ፖለቲከኞች በዚሁ መድረክ ታይተዋል ።*
> *የሚያነቡ እግሮች ገጽ 25*
>
> *. . . ስለሆነም ቀይ ሽብር በተፋፋመበት ወቅትና ከዚያም ወዲህም በኋለኞቹ ዓመታት በግቢው ውስጥ የተሾሙት ካቦዎች የምርመራውን ሂደት ከማጥበቅ አንፃር ተገቢውን ቁጥጥር በማድረግ በታማኝነት ያገለግላሉ ተብለው እምነት የተጣለባቸው ሲሆኑ ከተቃዋሚው ጎራ ያልመጡ ፣ለመንግሥት ታማኝ ናቸው ተብለው የሚገመቱ ፣ በሥረዓቱ ውስጥ ከመንግሥት ጋር ወግነው በሕዝብ ላይ በደል ያደረሱ ወዘተ የሚገኙባቸው ነበሩ ።ለአብነት ያህል የሚከተሉትን የማዕከላዊ ካቦዎች መመልከቱ ይህንን ያረጋግጥልናል ።*
>
> *የሚያነቡ እግሮች ገጽ 27-28*
>
> ***አስር አለቃ ገበየሁ ሁሴን ፡-*** *የትራፊክ ፖሊስ የነበረ ነው። በጉቦ ምክንያት ተጠርጥሮ የተራሰረ ስለመሆኑ የሚነገርለት ሲሆን በማዕከላዊ ቆይታው በመርማሪዎቹ ተመርጦ የግቢው ብቸኛ ፈላጭ ቆራጭ ካቦ ሆኖ አራመኔውን መርማሪ ሃምሳ አለቃ ተሾመ ባዮን ጓዶቹን በመርዳት አገልግሏል ።. . .*
>
> ***እሸቱ ሽንቁጤ*** *፡ - የብርሃነ ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኛ የነበረና በቀይ ሽብር አራማጅነቱ የሚታወቅ ግለሰብ ሲሆን 1972 ካቦ ሆኖ አግልግሏል ። ከአብዮቱ ወገን ነው የመጣሁት ብሎ የሚያስብ ነበር ።. . .*
>
> ***ትዕዛዙ ይልማ*** *፡ -. . . በጨካኝነቱ የሚታወቅና ውቃው የሚባል ቅፅል ስም የተሰጠው የመርማሪ ተፈራወርቅ አያሌው ታማኝ ተላላኪ በመሆን አግልግሏል ።. . .*
>
> ***ደረጀ ረጋሣ*** *፡ - . . . ከ1967 ጀምሮ በደርግ ቤተመንግሥት ውስጥ የሠራ ወታደር ነው ።ቤተመንግሥቱ ውስጥ በተደረጉ ግድያዎች ላይ መሣተፉ ይነገርለታል ። በእስር ቤት ውስ እራሱን እን አንድ አብዮተኛ በመቁጠር ለመርማሪዎች እየዋሸ ብዙ ሰዎች እንዲሰቃዩ ያደረገ ነው ።* [5]

በዚህ ግምገማ በጥቂቱ አንዳንዶቹን ልጥቀስ እንጂ በመፅሐፉ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ግለሰቦች ከሠሯቸው ግፎች ጋር ተጠቅሰዋል ።የሰው ሥቃይ የሚያስደስታቸው ፋሽሽቶች በአብዮትና ጸረ አብዮት ፍትጊያ ውስጥ በሰዎች መሰቃየት የግል ደስታቸውን ያገኙ ነበር ።ለምሳሌ ያህል የሃምሳ አለቃ ተሾመ ባዩ ቀን ብቻ ሳይሆን ሌሊትም ጭምር መኖሪውን በእሥር ቤቱ ውስጥ አድርጎ እንደነበር በመጽሐፉ የተጠቀሰ ነው። በሃገሪቱ ውስጥ የነበሩት ፋሽሽቶች ሁሉንም በስም ለመጥቀስ ያዳግት ይሆናል ። ግን በማዕከላዊ እስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ወንጀል የፈፀሙት ለምሳሌ ያህል መጥቀስ ይቻላል። -

> ***የሃምሳ አለቃ ተሾመ ባዩ ( በኋላ መቶ አለቃ )***
>
> *ቀይ ሽብር በተፋፋመበት በ1969 እና በ1970 ዓ. ም. እነ ኮሎኔል ተክለ ሚካኤል አርምዴ እና ሻለቃ ንጋቱ ገብረ ፃዲቅ የፖሊስ ሠራዊት ልዩ ምርመራ (ማዕከላዊ ) ሹመኞች በነበሩበት ጊዜና እና ሃምሳ አለቃ አደመ መኮንን ፣ መቶ አለቃ ገብረ ሚካኤል ፣ ሃምሳ አለቃ አለማየሁ ሙሉጌታ ፣ መቶ አለቃ ሰለሞን አያሌው ፣ ሻምበል ዋቀዮ ጃራ ፣ ምክትል አስር አለቃ ካሳሁን ደምሴ ፣ መቶ አለቃ*

ባድማ ንጋቱ ፣ መቶ አለቃ ተከስተ ተገኝ ፣ ሃምሳ አለቃ ሙላቱ ግዛው ፣ ወዘተ የተባሉ መርማሪዎች በነበሩበት ወቅት ከዋነኞቹ ዝነኛ መርማሪዎች አንዱ ነበር ።

ተፈራ ወርቅ አያሌው

ተፈራወርቅ አያሌው ኮሌኔል ለገሰ በላይነህና ኮሌኔል አርጋው እሸቴ የማዕከላዊ ምርመራ ኃላፊዎች ሆነው በተሾሙበት በ1970 ዎቹ ውስጥ መርማሪ ሆኖ የሠራ ነው ።

ተከሌ ወንድምአገኝ

ዓይነ ስውሩ የክፍሉን ግድግዳና እስረኞቹን እየደባበሰ በሩ ጋ ደርሶ ወጣ ሲል ፣ በያዘው አጭር የብረት ዱላ ማጅራቱን ላይ መታው ተንገዳግዶ ከመውደቅ ለመዳን ሲወራጭ ተከሌን እንቅ አደረገና ዝቅ በማለት በሁለት እጁ ብልቱን ግጥም አድርጎ ያዘው ። የዚህን ጊዜ ተከሌ "እረ ጎበዝ ፣ይዞኛል እኮ" ብሎ ሲጮህ እነዛ ሁለት ወጠምሻዎች ግራና ቀኝ ጉሮሮውንና ሽንጡን መትተው በመዘረር ተከሌን አስለቀቁት ። ተከሌ በሽንጡ ላይ የነበረውን የሰሜን ኮርያ የጎሪላ ጩቤ መዞ ዓይነ ስውሩን ጉሮሮውን እንደ ዶሮ ቀላው ዓይነስውሩም ምራቁን እንኳ ሳይውጥ ሕይወቱ አለፈች ።

ወታደር እሸቱ ወንድሙ ወ. ሥላሴ ፣ሕይወት በመንግስቱ ቤተመንግሥት ገጽ 142
የሚያነቡ እግሮች ገጽ 61 - 62

በእግዚያብሔር ይዣችኋለሁ ! እኔ የማውቀው ነገር የለም ። እኔ የሰባት ቤተሰቦች አባት ነኝና ነገሩን አላውቅም ሲል ፣ ተከሌ ነጭ የላስቲክ ጓንት በእጆቹ አጥልቆ ነበርና ያንን የፈነዳ እግሩን ቁስል በጫማው ሲረግጠው ፣የምርመራው ክፍል ሹም ደግሞ ደረቱን ላይ በእግሩ ረግጦ አትናገርምና አትድንም ? አለው ።

"እግዚያብሔርን ! የማውቀው  ነገር የለም ሲል፡ ተከሌ ከሽንጡ ሥር ትንሿን ጩቤ መዞ በጉሮሮው ላይ ሰካበትና ነቅሎ ደግሞ በደረቱ ላይ ቁልቁል ቀረቀረበት ። ጩቤውን ስቦ በማውጣት በሟች ሆድ ላይ ጠረግ ጠረግ አድርጎ ወደ ሽንጡ መለሰና ሁለቱንም ሰውየውን ሲመለከቱት ባንዴ ድርቅ ብሏል ።

ተከሌ እግሩን ፣ የምርመራ ክፍል ሹም እጁን ይዘው ከእስር ቤት ግቢ አውጥተው የቀድሞዎቹ  ሰዎች አስከሬን ላይ ደርበው ወደ መስክ ሄዱ ።

(ወታደር እሸቱ ወንድሙ ወ. ሥላሴ ፣ሕይወት በመንግስቱ ቤተ መንግሥት ገጽ 145)
የሚያነቡ እግሮች ገጽ 61 - 62

እነዚህ ዓይነት መርማሪዎች ናቸው አንድ ትውልድ የጨረሱት ። ዛሬ የደርግ መንግሥት ከወደቀ በኋላ እንዲህ አድርጌ ይህንን ያህል ዜጎች አላግባብ ገድያለሁ ብለው የፃፉ፣የተናዘዙ፣ንስሐ የገቡ የሉም ። ይባስ ብለው መግደላቸውን ፣ ማሰቃየታቸው ትክክል ነበር ብለው ሕዝብን ሊያሳምኑ የሚፈልጉ ሆነው ነው የሚገኙት ።

የደርግ መንግሥትን የሚደግፉ በተለያየ ቦታዎች ቀይ ሽብር መደረጉን ባይክዱም ደርግ በአዋጅ ደረጃ ቀይ ሽብርን አልጀመረም የሚሉ አይታጡም ። ከቀይ ሽብር በፊት ብዙም ያልተነገረለት ግን ብዙ ወጣቶችን የፈጀው **"ነፃ እርምጃ "** እንደ ነበረ ገና ብዙ ያልተነገረለት ወይም ያልተፃፈለት ነው ። **"ነፃ እርምጃ"**  የደርግ ደጋፊዎች በመኪና እየተዘዋወሩ የመንግሥት ተቃዋሚ የሚመስሏቸውን (ይህ በአለባበስ ፣ በመልክ ፣ በፀጉር ሁኔታ ሊሆን ይችላል )በጥይት እሩምታ የሚረሽኑበት ወቅት ነበር ። በወቅቱ ነፃ እርምጃን ያካሂዱ የነበሩ የመኢሶን ብሎም የደርግ ደጋፊዎች በዚህ ተግባር ላይ የፈጁትን ሕዝብ ቁጥር ሊያጋልጡ ይገባል ። ይህንን **መልክንና አለባበስን በማየት የሞት ፍርድ መፈፀምን** በሚመለከት አንዳንዶቹ ዛሬ በነጻው ዓለም በድሎት የሚገኙት የኢማሌድህ ድርጅት (***ኢማሌድሕ =የኢትዮጵያ ማከሲስታዊ ሌኒኒስታዊ ድርጅቶች ሕብረት በመባይ የሚታወቀው ሲሆን ያቀፋቸው ድርጅቶች ፣ መኢሶን ፣ ኢጭአት ፣ ወዝ ሊግ ፣ማሌሪድ ፣ አብዮታዊ ሰደድ ናቸው ።እነዚህ ድርጅቶች የደርግ ደጋፊ በመሆን ጭፍጨፋውን አካሂደዋል**) አባሎች በተለይም የመኢሶን አባላት መሆናቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚዘነጋው አይደለም ።

ዛሬ ደጋፊዎቹ ባዘጋጁለት መድረክ የሚንዘባነነው መንግሥቱ ኃይለ ማርያም  በሙታን ላይ ያሹፍ እንጂ ለዚህ አሳፋሪ ተግባር በጠርሙስ ቀይ ቀለም እየደፋ ሲፎክር እንደነበረ ከፎቶግራፉ መረጃ ጋር የቀረበ ነው ።

በ1969 እና በ1970 ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠረው ከፍተኛ ፖለቲካዊ ውጥረት ምክንያት በመንግሥቱ ኃይለማርያም የሚመራው የደርግ መንግሥት ተቃዋሚ ቡድኖች ለመደምሰስ ሲል በይፋ ቀይ ሽብር ያወጀበት ጊዜ ነበር ።ሌ.ኮሌኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ራሳቸው በቀይ ቀለም የተሞላ ጠርሙስ በተምሳሌነቱ አብዮት አደባባይ ላይ በመከስከስ ከጥር 24 ቀን 1969 ዓ.ም. ጀምሮ ለተከታታዮቻቸው የግድያ ትዕዛዝ በመስጠታቸው እና ቀጥሎም ጥቃት ለማድረስ የሚያደፋፈፍር ሁኔታ በመመቻቸቱ ምክንያት "ነፃ እርምጃ " የተባለውን ድርጊት እየተስፋፋ መጥቶ መላው ሃገሪቱ በደም እንድትቀላ ሆናለች ።

የሚያነቡ እግሮች ገጽ 42-43

ይህንን የግፍ ዘመን  ሲያገለግሉ የነበሩ መንግሥታዊ መዋቅሮች ውስጥ የሚሠሩ ፋሽሽቶች ተደጋግፈውና ተባብረው የሚሠሩ ሲሆኑ በተለያየ ቦታ ላደረሱት ጥፋት የተሟላ መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነ የታመነ ነው ። ዛሬ በየተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጥ እንኳ ሳይቀር የተሰገሰጉትን ለይቶ ለማወቅ አዳጋች የሆነበት ምክንያት በመረጃ ደረጃ የተጋለጡና ለሕዝብ ማንነታቸው የሚታወቀው የብዙዎቹ አይደለም ። በተለይ የደርግ መንግሥት በሚወድቅበት ወቅት ለፖለቲካ ትምህርት ወደ ምሥራቅ አውሮፓ ሄደው የነበሩት ዛሬ በምዕራብ አውሮፓ ከነሠሩት ወንጀል በምቾት ተቀምጠው ይገኛሉ።

ቀይ ሽብርንም ይሁን ነፃ እርምጃን ያካሄዱት በድርጅት እንደነ መኢሶን ፣ኢጭአት ፣ ማሌሬድ .ወዝ ሊግና ሰደድ ሲሆኑ በመንግሥት መዋቅር ደግሞ በመጽሐፉ ላይ የተጠቀሱት ፡ -

1. አብዮታዊ ቋሚ ኮሚቴ የሕዝብ ደህንነት ጉዳይ ሃላፊዎች
2. የአጠቃላይ መረጃ ማመዛዘኛ ማከፋፈያ ኮሚቴ
3. የሃገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር
4. የአብዮታዊ ዘመቻ ጥበቃ መምሪያ
5. የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴ
6. የቀበሌ የከፍተኛ ነዋሪዎች ማህበራት
7. የሕዝብ ድርጅት ጉዳ|ይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት
8. የደርግ የምርመራ ክፍል
9. የማዕከላዊ ምርመራ ድርጅት
10. የወታደራዊ ፖሊስ እስር ቤት
11. የቀይ ሽብር አስተባባሪ ኮሚቴ
12. የአብዮትና ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ
13. ልዩ ጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት
14. የእስረኞች አጣሪ ኮሚቴ
15. የአራተኛ ክፍለ ጦር ፣የ1ኛ ክፍለ ጦርና የ29ኛ ሻለቃ ጦር ሠፈር
16. የአዲስ አበባ ወህኒ ቤት

እነዚህ ከላይ ከአንድ እስከ አስራ ስድስት የተጠቀሱ የመንግሥት መዋቅሮች የገደሏቸው ፣ ያሰሯቸው ፣ ያሰቃዩዋቸው ፣ አካላቸውን  ያጎደሏቸው ቁጥር በውል አይታወቅም ።እንደ ሃገራችን አባባል "ቤት ይቁጠረው ፣ወላድ ትቁጠረው ብለን ካላለፍን በስተቀር ። እነዚህ ወንጀለኞች አንዳንዶቹ ባሁኑ ወቅት በነፃው ዓለም በደስታና በተድላ የሚኖሩ ሲሆኑ በሃገር አንድነት ስም ፣ በዘር ድርጅቾች ስም እንደገና ወደ ሥልጣን ለመመለስ የሚያደርጉት ጥረት በየፓልቶኩና በየድረ ገፁ የሚታይ ነው ። አንዳንዶቹም ዛሬ ለወያኔ በማገልግል ላይ ይገኛሉ ።

የደርግ ዓይነት ቀይ ሽብር እንዳይደገም ከተፈለገ እነዚህ ወንጀለኞች ለሕዝብ እንዲጋለጡ ማድረግ የሁላችንም ተግባር መሆን ይገባዋል ። ዛሬ  ሃራሬ ተቀምጦ ከሚዝናናው መንግሥቱ ጀምሮ ፣በጀርመን ሃገር የሚዝናኑት ዘለቀ በየነ (ጄነራል ) ፣ በቤልጅየም በነፃነት የሚኖረው ነገደ ጎበዜ ፣ ሰሜን አሜሪካ የሚገኘው አሰፋ ጨቦ ፣ ሆላንድ የሚገኘው ተስፋዬ መኮንን ሁሉም ለፍርድ የሚቀርቡበት መንገድ ሊተለም ይገባል ። ሌሎቹንም አጋጣሚው እስከሚፈቅድና ለፍርድ እስከሚቀርቡ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ እንወክላለን በሚሉ ድርጅቶች እንዳይሰለፉ ማድረግ ፣ ለተቃዋሚዎች አንድነት ፣ በሕዝብ ታማኝነት ለማግኘት ይረዳል ። ወያኔን ሃገር አጥፊ ነውና ሁሉንም አስተባብረን መጓዝ አለብን የሚለው መፈክር ሊሠራ የሚችለው እነዚህ ግፈኞች ጥፋታቸውን አምነው እውነተኛ የሆነ የሕዝብ ብያኔ ሲቀበሉ ነው ።

ልዩ እስር ቤቶችና ማሰቃያ ቤቶች በሃገሪቷ ውስጥ በተቋቋሙበት ወቅት ከማዕከላዊ ሌላ የታወቁ የመግደያና የማሰቃያ ማሽኖች ተቋቁመው ነበር። ለምሳሌ **ቤርሙዳ የሚባለው በ1970 ሁለተኛ አጋማሽ ለምርመራ ተግባር በከፍተኛ 23 ቀበሌ 12 ውስጥ የሚገኝ ቪላ ቤት ነው ።** ወደ እዚህ እስር ቤት እስረኞች ከመምጣታቸው በፊት የሚሄዱበትን እንዳያውቁ ዓይናቸው ታስሮ ነው ። ይህ ቪላ ቤት ውር ውር ከሚሉት ተናካሽ ውሾች ፣እየሰከሩም ቢሆን ከሚገርፉ መርማሪዎችና እስረኛው ከቤት ወጥቶ ውርጭ ላይ እንዲያድር ሲደረግ በላዩ ላይ በባልዲ ውሃ ሞልተው በመድፋት የማሠቃየት ድርሻ ከነበራቸው የጥበቃ ሠራተኞች በስተቀር ቁጥሩ ብዙ የሆነ እሥረኛ አልነበረበትም ።  በዚህ የሚያነቡ እግሮች በሚለው መጽሐፍ ውስጥ በሰፊው ተፅፎለታል ።

ከእስር ቤቶች ሁሉ አሰቃቂ ከነበሩት ውስጥ ደርግ ጽህፈት ቤት የምርመራ ክፍል በኢትዮጵያ የግፍ ታሪክ ውስጥ ትልቁን ቦታ ይዞ ይገኛል ። የሃገሪቱ መሪ በሚገኝበት በደርግ ጽሕፈት ቤት ውስጥ የሚገኘው ይህ ዜጎችን የማሰቃያ ቦታ የሃገሪቱን ብሩሕ ተሰፋዎች የተጨረሱበት ነው ። ታዋቂው ፋሽሽት ሻምበል ብርሃኑ ከበደ ይህንን የግፍ ፋብሪካ ነበር

የመራው ። " ሃገር ወዳዱ" መንግሥቱ ኃይለ ማርያም፣ "ዝንብ ገለው"የማያውቁት መንግሥቱ ኃይለማርያም ከዚህ የግፍ መቀፍቀፊን ይፈጽም የነበረውን ግድያ አላውቅም ማለት ቀድሞ በግድያው ላይ ከመሣተፍ ያልተናነሰ በሕዝብ ላይ ተደጋጋሚ በደል መፈፀም ነው ።ሰለዚህ እስር ቤት እሸቱ ወንድሙ በመጽሐፉ ገጽ 76 የጠቀሰውን ግርማይ አብርሃ እንደመረጃ አቅርቦታል ።

**ማማዬ ላይ ሆኜ ሁኔታውን ስመለከት ድንገት ድንግርግር ብሎኝ ሳለሁ ፣ያቺ አንድ ቁጥር የተጣለችው አራስ ከነልጇ ትዝ አለችኝና ቀና ብል ሻለቃ ጌታቸው ሺበሺና ሁለት ሰማያዊ ቱታ ለብሰው ጠፍጣፋ ብረት የያዙ ወታደሮች ወደ እስር ቤቱ ግቢ ዘው አሉ ። ዘብ ሃላፊው የመግቢያውን  በር ተደግፎ በዝምታ ያያቸዋል ።**

**ሻለቃ ጌታቸው ሽበሺ ክፉኛ ተናደዋል ጭካኔያቸው በፊታቸው ላይ ይነበባል ። መሬቱን ረገጥ አደረጉና  " ተነስተሽ አትሄጂም " አሏት ሴትየዋ ፅንሱን አቅፋ እንደ ምንም ቀና ብላ ለመቆም ስትንገዳገድ የያዘችው ፅንስ ወደቀባት ። ለማንሳት ጎንበስ ስትል ሰማያዊ ቱታ የለበሱት ወታደሮች እጃቸውን ሽንጣቸው ላይ አድርገው የፌዝ ፈገግታ ሲለዋወጡ ሻለቃ ጌተቻው ሽበሺ " ሴትዮ ! የሰው ሥጋና ደም አብዮቱን ያጠናክረዋል እንጂ ምን ይለዋል ብለሽ ነው ? እርገጪውና እለፊ !" ብለው እንደ መብረቅ ሲጮሁባት ተዝለፍልፋ ፅንሱ ላይ ወደቀች ። በዚያ ገጀራ መሰል በሆነ ብረት ማጅራቷን ፣ጆሮ ግንዷን ሥር ደጋግመው መቷትና በእግራቸው ገልበጥ አድርገው ገጀራውን ሆዷ ላይ ሰኩባት። ከዚያም እነዚያ ገጀሪስቶችን በእጅ እየጠቆሙ "በሏት ፣በሏት፣ በቃ በሏት " ብለው ትዕዛዝ እንደሰጡ እነዚያ ሁለት ቱታ ለባሾች እርሷንና ፅንሷን ቀጠቀጧቸው። ከዚያም ሻለቃ ጌታቸው ሽበሺ " መኪናው ሲመጣ ይዟቸው ይሂድ " የሚል ትዕዛዝ ሰጡና ራመድ ራመድ ብለው ከእስር ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወጡ ።**

**እሸቱ ወንድሙ፣ሕይወት በመንግስቱ ቤተ መንግሥት ገጽ 76**
**የሚያነቡ እግሮች ገጽ 66**

ይህንን ለዓይነት አቀረብኩት እንጂ በሚያነቡ እግሮች ውስጥ ይህንን የመሳሰሉ አስገራሚና ዘግናኝ ታሪኮች በሰፊው ይገኛሉ ።መረጃዎቹ የሚያስገርሙና በዓይነታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በገሃድ የወጡ ፣ወይም ለሕዝብ እይታ የበቁ  ሲሆኑ በዛ የመከራ ዘመን ያለፉ በሙሉ ታሪካቸውን እንዲጽፉ ይገፋፋል ። በተለይ በመጽሐፉ ውስጥ 1975 እና 1978 ላይ በምህረት የተፈቱትን እስረኞች ስም ዝርዝር ፣ አብዮቱን ሊያደናቅፉሉ ይችላሉ ተብለው የታሰሩ የልዑላዊያን ቤተሰብ አባላት ፣ የመኢሶን ፣የኦነግ ፣ የህወሐት ፣የህግሓኤ የኢሕድን ፣ የተሓኤ አባላት ናችሁ ተብለው የታሠሩ ስም ዝርዝር በውስጡ ይዟል።ይህንን ለወደፊት ታሪክ ጸሐፊዎች ጠቃሚ መሆኑ አይጠራጥርም ።

በዚህ በትንሽ ግምገማ 426 ገጽ የያዘን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉ መዳሠስ አይቻልም ። መጽሐፉን ገዝቶ ማንበብ አስፈላጊ ነው ። በዚሁ አጋጣሚ የዚህን ወብ የሆነ መጽሐፍ ጸሐፊ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን እያቀረብኩ ሌሎችም እስከ አሁን ተደብቀው የሚገኙትን እውነተኛ ታሪኮች እንዲጽፉና መጪው ትውልድ ያንን የመሰለ አሳፋሪ ታሪክ እንዳይደገም እንዲታገል ያደርጉ ዘንድ ጥሪዬን አቀርባለሁ ።

በመጽሐፉ ላይ የጸሐፊው አድራሻ ስላልተጠቀሰ ይህንን ግምገማ ልልክለት አልቻልኩም ። በግል የምታውቁት ካላችሁ እንድታስተላልፉልኝ አደራ እላለሁ ።

beljig.ali@gmail.com

በዛ ግፍ ዘመን ስለተሰቃዩ የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም !!!
በልጅግ አሊ ------ መስከረም 2003